# የሞት ፍልስፍና በተመረጡ የአማርኛ ግጥሞች ውስጥ

ደሳለኝ ሥዩም ፈለቀ*

**አጠቃሎ፦** ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ከአራት የግጥም ሥራዎች የተመረጡ አራት ግጥሞች ላይ ነው፡፡ ግጥሞቹ ነቢይ መኮንን፤ ፀሐይ መላኩ፤ አበባው መላኩና አንዷለም አባተ ጸጋዬ ገብረ መድኅንን ለመዘከር የገጠሟቸው ግጥሞች ናቸው፡፡ ግጥሞቹ ሊመረጡ የቻሉት ሞትን በፍልስፍና ዕይታ በማዬታቸው ለጥናቱ ጉዳይ ቀጥተኛ ተተኳሪ ሊሆኑ በመቻላቸው ነው፡፡ በጥናቱ የተፈተሹት፤ የተመረጡትም ጉዳይ-መር (purposive) ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ ገጣሚዎቹ ምን ዓይነት የሞት ፍልስፍናን እንደሚከተሉ ማሳዬት ነው፡፡ በጥናቱ ማረጋገጥ እንደተቻለው አራቱ ገጣሚያን የተለያዩ የሞት ፍልስፍናዎችን ይከተላሉ፡፡ ፍልስፍናቸውም ‹ከሞት በኋላ ሕይወት› እና ‹ሞት የመጨረሻ› በሚሉት ሁለት ጥቅል የሞት ፍልስፍና ጥላዎች ውስጥ ማረፍ ቢችሉም ገጣሚያኑ የየራሳቸው ዝርዝር የሞት ፍልስፍና እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ቁልፍ ቃላት፡- ግጥም፣ ፍልስፍና፣ ሞት

## መግቢያ

ይህ ጥናት የሁለት ታላላቅ ሙያዎችን የዕይታ መነጽር የሚጠቀም ነው፡፡ የፍልስፍና እና የሥነ ጽሑፍን፡፡ ፍልስፍና እና ሥነ ግጥም ትላልቅ ሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰፋፊ የጥናት መስኮችም ናቸው፡፡ ሁለቱን በነጠላ ማጥናት አንድ ነገር ሆኖ ሁለቱ በጋራ የሚያተኩሩባቸውን ነጥቦች እና የጋራ መገለጫዎች ማጥናትም የአጥኚዎችን ፍላጎት እየማረከ ያለ ርእሰ ነገር ነው፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚ ይሄንን ርእሰ ጉዳይ ለማጥናት ሲነሣ በርእሰ ነገሩ ላይ የተሠሩ ጥናቶች ካሉ መዳሰሱ አልቀረም፡፡ ነገር ግን አጥኚው ባደረገው የቤተ መጻሕፍት እና ኤሌክትሮኒክ ቤተ መጻሕፍት ቅኝት በርእሰ ነገሩ ላይ የአማርኛ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን ተንተርሶ የተሠራ አንድም ጥናት ማግኘት አልቻለም፡፡

ለምን አልተጠናም የሚለውን ለማወቅ ማጥናት የሚገባ ሆኖ ርእሰ ነገሩ ግን ለጥናት በቂ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡ ለምን ቢሉ ሥነ ግጥም ፍልስፍና ለመሆን የሚችለውን ያህል ፍልስፍናም ግጥማዊ መሆን ይችላልና፡፡ ለምሳሌ በሼክስፒር ግጥማዊ - የተውኔት ሥራ ውስጥ ፍልስፍና የመኖሩን ያህል በፕሌቶ ፍልስፍናዊ ሥራ ውስጥ ደግሞ ግጥማዊነት አለ፡፡ ጸጋዬ ገብረ መድኅን በተረጎመው በሃምሌት ውስጥ የሚገኝ የጸሐፌ ተውኔት ሼክስፒር ሐሳብ ይኸውና

መሆን ወይም አለመሆን እዚህ ላይ ነው ችግሩ
የእድል የፈተና አለንጋ ሲወናጨፍ ወስፈንጥሩ
በሐሳብ ግርፊያ መሰቅዬቱን ችሎ ታፍኖ ማደሩ?
ወይስ የመከራን ማዕበል ተጋፍጦ ጦርን ከጦሩ
ተጋትሮ ወግቶ ድል መምታት እስኪነቀል ከሥሩ
የቱ ነው ለሰው ልጅ ክብሩ? (ጸጋዬ 1964፡55)

በዚህ የስንኝ ድርድር ቃለ ተውኔት ውስጥ ደራሲው ዲበ አካላዊ የህልውና ትርጓሜ ጥያቄን ያነሣል፡፡ ይህ ጥያቄ ደግሞ ፍልስፍናዊ ነው፡፡ ዲበ አካላዊ ዕይታ ደግሞ ፍልስፍና ነው፡፡ ለዚህ አስረጅ ሊሆነን የሚችል የመሆን፣ የትርጉምና የእርባና ፍልስፍናዊ ጥያቄ እንጥቀስ፤ The question 'why are there beings at all instead of nothing?' Is first in rank for us as the broadest, as the deepest, and finally as the most original question. (Heidegger 2000:2) የሚለው የሃይዲገር ሐተታ በፍልስፍና ውስጥ ትልቁ፣ ሰፊው እና መሠረታዊ ጥያቄ ዲበ አካላዊ የሆነው ‹‹የመሆን አለመሆን›› ጥያቄ መሆኑን ያስረዳናል፡፡ ሼክስፒርም በሀምሌት ስንኞች ውስጥ የሚነገረን ይሄንኑ ነው፡፡ ይሄ ገጣሚዎች በሥራቸው ውስጥ ፍልስፍናዊ ነገር እንዳላቸው

* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪ።

የሚያሳየን እውነት ሲሆን በፈላስፎችም ሥራዎች ውስጥ ግጥማዊነት እንዳለ አስረጅ መጥቀስ እንችላለን።

ለምሳሌ ፕሌቶ በ ‘Republic’ ገጽ 19 ላይ እንዲህ የሚል ገለጻ አለው: I turned round, and asked him where his master was. There he is, said the youth, coming after you, if you will only wait†. ይሄን ፍልስፍናዊ ገለጻ በቀጣዩ ግጥማዊ ገለጻ እናገኘዋለን፦

I turned round
and asked him
where his master was.
There he is,
said the youth, coming after you,
if you will only wait.
ዘወርወር እላለሁ
እጠይቀዋለሁ
ወዴት ነው አለቃህ?
ያ…ው አለኝ ወጣቱ
ታግሰህ ከቆዩህ
በስምህ ሚመጣ አለና ከኋላህ
ታስተውለዋለህ

ምንም እንኳ ራሱ ፕሌቶ “there is an old quarrel between philosophy and poetry” (Republic 607b5—6) በማለት ገጣሚ አይደለሁም ለማለት ቢሞክርም የዘርፉ ባለሙያዎች ግን ሥራው ግጥማዊ መሆኑን “Plato unlike Arstotle, was a poet”. (Sir A. quoted In Hartland) በማለት የፕሌቶን ገጣሚነት መናገር ችለዋል። ስቱዋርት ደግሞ በፕሌቶ ሥራ ውስጥ ግጥምና ፍልስፍና በአንድ መግጠማቸውን ይገልጻሉ። Philosphy and poetry (are) blended together where Plato is at his highest — in his Myths (Stewart IBID) ፕሌቶ ራሱ ገጣሚ አይደለሁም እያለ፤ አንባቢያኑ ደግሞ ፕሌቶ ገጣሚ ነው በሚሉበት ዐውድ ውስጥ የገጣሚነቱ ጉዳይ የሚያነጋግር አለመሆኑን ደግሞ ሃርትላንድ በአንድ ድርሳናቸው ላይ አትተዋል። That Plato was in same sense a poet is which most of us are prepared to recognize without much hesitation (Hartland 1951:1)። እንዲህ ባለው ክርክር ውስጥ የምናገኘው አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም ፍልስፍና ከግጥም ግጥምም ከፍልስፍና ጋር እንደሚዛመድ ነው። ስለዚህም ከላይ ባዬናቸው አስረጅዎች መሠረትነት ሁለቱ ሙያዎች የሚያዛምዳቸው ነጥብ ወይም የጋራ የሆነ አትኩሮት እንዳላቸው ልብ ለማለት ይቻላል።

ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ ውበታዊ፣ ፍልስፍናዊ ሥራ ደግሞ ይዘታዊነታቸው ጎልቶ የሚታይም ቢሆን ቅሉ የአንዳቸው መገለጫ በሌላኛቸው ላይ የሚገኝ ነው። ‘Thoughts without content are empty, and intuitions without concepts are blind’ (Kant 1898:93) ውብታዊነት ከይዘት ውጭ ይዘታዊነትም ከውበት ውጭ የማይሆንበትን ሂደት በፍልስፍና እና ግጥም ውስጥ እናገኛለን።

ሥነ-ጽሑፍና ፍልስፍና ይገናኛሉ ካልን ታዲያ የሥነ-ጽሑፍ ዘር የሆነው ግጥም እና ፍልስፍና እንዴት ላይገናኙ ይችላሉ? ታዲያ ግጥምና ፍልስፍና ይገናኛሉ ማለት ግጥም የሞከረው ፈላስፋ ፍልስፍና የሞከረው ገጣሚ ናቸው ማለት አይደለም፤ ይነካካሉ፣ ይገናኛሉ ማለት እንጅ። ይህ ጥናት አንድ ዐይንን ወደ ፍልስፍና አንድ ዐይንን ወደ ግጥም በማድረግ ለመመልከት የሚሞክር ነው። የሞት ፍልስፍና ላይ ከጥንት እስካሁን የተነሱ ፈላስፎች ብዙ ፍልስፍናዊ ሐሳቦችን አራምደዋል። አስቀድሞ ከጥንት እስከዛሬ በዓለም ፈላስፎች ዘንድ ሞት ምን ዓይነት አተያይ ነበረው የሚለውን

† የአማርኛ ትርጉሙ ‹‹ ዘወር ዘወር አልኩ፤ እንዲህም አልኩት፤ አለቃህ በወዴት አለ፤ ወጣቱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ እስኪመጣማ ከቆየህ በስምህ የሚመጣው እርሱ ነው››

አደራጅቶ ቅርጽ አስይዞ ማቅረብ ተገቢ ይመስላል። ስለዚህም አስቀድመን ፈር ለመያዝ እንዲያመቹን የሞት ፍልስፍናዎችን እንቃኛለን።

በዚህ ጥናት ውስጥ ለመመልከት የመረጥኳቸው ግጥሞች የተመረጡበት መሥፈርት ‹ጉዳይ መር› *ፐርፐሲቭ* መንገድን በመጠቀም ነው። ስለዚህም ድጎረ 97 (የጸጋዬ ገብረ መድኅንን ዕረፍት ተከትለው) የታተሙ ሆነውም ገጣሚዎቹ ከአንድ በላይ መጻሕፍትን ያሳተሙ ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ የታተሙ ወይም በአንድና በተጨማሪ ሌሎች ሥራዎች የተሳተፉ የሚል መስፈርት በማስቀመጥ ለምመለከተው ፍልስፍናዊ ጉዳይ የሚጠቅሙኝን ግጥሞች መርጫለሁ።

ምክንያቱም ግጥሞቹ የሞት ፍልስፍና (Philosophy of death) ላይ ተጨማሪ ጠጠር የሚያቀብሉ፣ የጠራ አቋም የሚያራምዱ፣ ይሄ ነው የተባለ ሙግት የሚሞግቱ መሆን አለባቸው። እዚህ ላይ ‹ይሄ ነው የተባለ ሙግት› ስለመሆኑ እንዴት መዘንክ?› ጥያቄ ሊሆን ይችላል፤ የእኔም ምላሽ የሚከተለው ነው።

በፍልስፍና ውስጥ ሞት አንድ ፍልስፍናዊ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ሞት ፍልስፍናዊ ርዕሰ ጉዳይ መሆን የቻለው ወሳኝ የህይወት ሁነት ከመሆኑ በተጨማሪ የሰውን ምንነትና የትመጥነት (The Metaphysics of human being) የሚወስን፣ የሚያስረዳ እና የሚያወዛግብ በመሆኑ ፈላስፎች አንድ የመከራከሪያ ቁም ነገር ያደርጉታል። ታዲያ መከራከሪያ ሲባል የቃላት ጋጋታ እና የስሜት ድንፋታ ሳይሆን ርስ በርሱ የሚመጋገብ፣ ተያያዥነት ያለው አስረጅ አመክንዮን ማቅረብ ነው። የፍልስፍና መንገዱ ይሄው ስለሆነ።

በዚህ መሠረት የፀሐይ መላኩ ‹ሞተ እኮ የሚለው ይሙት› (1999) የአበባው መላኩ ‹አባታለም ጸጋዬ (2000) የአንዷለም አባተ ‹አንድ ፀሐይ› 1999፣ የነብይ መኮንን ‹ለካ ሞት ግጥም አይችልም› 1998፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ተዳስሰዋል።

## ጽንሰ ሐሳቦች

### *ሞት መጨረሻ አይደለም*

የምንኖርበት ዓለም ያልተሟላ፣ የእርኩሳን ፈተና ያለበት፣ ስቃይን ያዘለ ከመሆኑም በላይ መጨረሻው በሞት የሚደመደም ነው። ሞት ማንም እርግጠኛ ሊሆንበት የሚችለው ብቸኛ እውነት ነው (Frankl 1984:96) እዚህ ጋ ነው ጥያቄው፤ የእኛ ህይወት ማለት ያልተሟላን ኑሮ መኖር ነውን? ሞትስ ልናመልጠው የማንችለው የሁላንችንም እጣ ፈንታ ነውን?

ሰው የትም ይኑር፣ በየትኛውም ባህል ይቀረጽ ለዚህ ጥያቄ እርግጡን ይመልሳል ብሎ ማሰብ አይቻልም፤ ቢያንስ ያለፉትን ዘመናት ህይወቱን አይተንበታልና[‡]። ከጥንታዊያን ግሪኮች ሄዴዝ[§] (Hades) እስከ ዘመናዊው የክርስትና ገነትና ሲኦል ምልከታ ድረስ ህይወት በምድራዊ ኑረት ታብቃለች ተብሎ አይታሰብም። ይሁንና ከዚህ ህይወት በኋላ ሌላ ህይወት አለ፤ ሞትም የመጨረሻ አይደለም በሚለው ምልከታ ውስጥ ደግሞ ልዩ ልዩ ዓይነት የቀጣይ ሕይወት ብያኔዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ ብያኔዎች አንደኛው መንገድ ከዚህ ሕይወት በኋላ ዳግም መፈጠር (Re-incarnation) ይቀጥላል የሚል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሕያውነት (Re-surrection) ነው። የመጀመሪያው ምልከታ ሰው ሆኖ የሞተ ሌላ ተክል ወይም እንስሳ ሆኖ ይመጣል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በእግዚአብሔር ዓለም ዘንድ ዘላለማዊ ህይወትን የሚቀጥለው የሰው ልጅ ነፍስ የዚህኛው ዓለም ሞቱ ወደ ቀጣዩ ዓለም ሕይወት የሚሸጋገርበት ነው። በየጥቂቱ እንዘርዝር!

### *ዳግም ውልደት (Re-incarnation)*

[‡] ክርስቲያን ይሁን ዋቄ ፈታ፣ ኢስላም ይሁን ኢ-አማኒ እስካሁን ያልታዩ ዓለም የለውም።

[§] በግሪክ ጥንታዊ አፈታሪክ ውስጥ ‹‹የታችኛው ዓለም አምላክ›› ተብሎ የሚታወቅ እንዲሁም የዘዩስ ወንድም እና የፐርሴፎን ባል የሚባል አምላክ ነው።

ከጥንታዊያን የሂንዱ (ህንድ) ሥነ-ጽሑፍ ጀምሮ ሲተረክ የመጣ ነው:: ነፍስ ከአንድ ፍጡር ስትወጣ የዚያች ነፍስ መጨረሻዋ ያ ሞት አይደለም:: ይልቁንም ሌላ ስጋን ይዛ የምትፈጠርበት ሌላ አጋጣሚ እንጅ:: ከሂንዱይዝም ወደ ቢድሂይዝም የተሻገረው ይህ እምነት ወደ ምዕራባዊያን ባህልነት ከዚያም ወደ ፓይታጎረሳዊያን ከዚያም ወደ ፕላቶንያን አስተምህሮዎች ሲሸጋገር ኖሯል:: የዚህ ፍልስፍና መሠረታዊ እሳቤዎች ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፤ አንደኛው የዳግም ውልደት ዑደት ሲሆን ሁለተኛው የነፍስ ኢ-መዋቲነት ነው::

በቡዲሂዝም የዳግም ውልደት ዑደት ‹ሳሚሳር› ተብሎ ይታወቃል፤ ትርጓሜውም ‹መደነቂያ› ማለት ነው:: ምንጩንና መሠረቱን ለማወቅ የሚያዳግት፣ ትርጉም አልባ፣ መጀመሪያው የማይታወቅ ረጅም ዑደት ነው ይሉታል:: ቡድሃ ሲገልጸው እንዲህ ነው፤ ሞት ወይም ዳግም ውልደት መገለጫዎች ናቸው፤ ተመሳሳይ ስሜትን እና ሁነትን የሚገልጹ:: የሰውን ልጅ ስቃይ፣ አለመርካት፣ እንግልት፣ ስጋት (ድሁካ ይሉታል በራሳቸው ቃል) እነዚህን የሚገልጽ ሲሆን እኒህም የሰው ልጅ ቋሚ ባልሆነ ሁነት ውስጥ በመኖሩ ምክንያት በየጊዜው በሚገጥሙት ለውጦች የሚከሰቱ ናቸው (Harvey 1990:32፣47፣48)

የዳግም ውልደት ነገር ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትና ህይወት ላላቸው ነገሮች በሙሉ ይሠራል:: በቡድሃ የዳግም ውልደት ነገር በሁሉም ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ላይ ያለ ነው:: ‹ፔታ› ብለው ከሚጠሩት የሲኦል አምሳል ተነስቶ ሃያ ስድስት ደረጃዎች እስካሉት የገነት አምሳል የሚደርስ ክፍፍል አለ:: የገነት አምሳል ክፍፍሉም ከህይወት ርዝማኔ፤ የህይወት ጣእም፣ እንዲሁም ነጻነት ጋር የተያያዙ ልዩነቶችን የያዘ ነው:: የሰው ልጅ የዳግም ውልደት ህይወት ጥራት የሚወሰነውም በሰውየው ቀዳሚ ህይወት ታሪክ ነው::

የሰው ልጅ ያማረ እድልን በዳግም ውልደት ጊዜ እንዲጎናጸፍ በመንፈሳዊነት የጎለበተ፣ በቅን አመለካከቱ የሰለጠነ፣ ለሰው እና ለመላው ፍጥረት ሁሉ መልካምን የሚከውን መሆን አለበት፤ ሳር ሆኖ ተወልዶ ከብት እንዳይግጠው፣ አህያ ሆኖ ተፈጥሮ ለጭነት እንዳይውል ሊታደገው የሚችለው ሁሉ የቀዳሚ ህይወቱ ቱሩፋትና ተዘክሮ ብቻ ነው (ዝኒከማሁ፡ 38)

በኋላ የመጡት የዓለማችን ፈላስፎችም እንዲህ ያለውን እምነት ሲያንጸባርቁ ታይተዋል:: ከፓይታጎረስ ተነስቶ እስከፕሌቶ የሄደው ይህ አይነቱ ፍልስፍና በተደራጀውና ቅርጽ ባለው ፍልስፍና ውስጥ ዳግም ውልደት ቅርጽ የያዘ ትንታኔ እንዲሆን አስችሎታል::

ፕሌቶ ፌዲዮ በሚለው ሥራው ውስጥ ነፍስ ኢ-መዋቲ መሆኗን ይሞግታል:: ከዚህ ነፍስ ኢ-መዋቲነት ላይ ተነስቶ ነው ፕሌቶ የዲበአካል ፍልስፍናው እና የሥነ እውቀት ንድፈ ሐሳቡ የሚነመጨው:: ለፕሌቶ ሞት ማለት የነፍስና ሥጋ መለያየት ነው፤ መለያየቱ እርግጥ ሲሆን ነፍስ ከስጋ ተላቃ በራሷ ሕያው ትሆናለች፤ ከስጋ ተጽዕኖ ነጻ የሆነችው ነፍስም በራሷ የምትቆም! (Benjamin 1952:223).

ፕሌቶ በዚህ ድርሳኑ አብዝቶ እንደሚሞግተው እያንዳንዱ ነገር ሁለት አጣማጆች አሉት:: እነዚህም አንደኛው ብልሽት (መጥፎ) እና ነገሩ የሚሠራበት አላባ (መልካምነት) ናቸው:: አንድ ነገር ተበላሽቶ ቢገኝ ወይም ቢከስም የዚህ ብልሽት ወይም ክስመት ምክንያቱ ከዚህ ነገር ጋር አብሮ በነበረው የብልሽት አላባ (አጣማጅ) የተነሳ ነው:: በመሆኑም ነፍስ በብልሽት ማለትም ግድ የለሽነት፣ ጨካኝነት፣ ጋጠ ወጥነት በመሳሰሉት የምትበላሽ ናት፤ ይህ ብልሽት ነፍስን የማትረጋ እና እርካታ የለሽ ያደርጋታል እንጅ ጨርሶ የሚያጠፋት ነገር አይደለም፤ ስለዚህም ነፍስ ኢ-መዋቲ ናት:: (ዝኒከማሁ:436)

ነገሮች በአጣማጅ ወይም በተቃርኖ የቆሙ ናቸው ብሎ ያምናል ፕሌቶ:: ለሞቃቱ ቀዝቃዛ ተቃራኒው ነው፤ ግን የቀዘቀው እንደሚሞቀው የሞቀው ይቀዘቅዛል:: ሞትም የህይወት ተቃርኖ ነው፤ ሞት የህይወት አዲስ ምዕራፍ ህይወትም የሞት አዲስ ምዕራፍ ነው:: ስለሆነም እንደገና መወለድ የሞት ተቃራኒ ነው:: የነፍስን ኢ-መዋቲነት ከሚመግቱት አንዱ ሶቅራጥስ የሆሜርን አባባል ተውሶ እንዲህ ይላል፤ ‹ከዝንጋኤ ወንዝ ጠጥተው (ያለፈውን ረስተው፣ በበፊቱ ስጋቸው ውስጥ የነበራቸውን ልምድ ሁሉ ረስተው) ፣ ነፍሶች እንደገና ይመጣሉ› (ዝኒከማሁ:436)::

## ሕያውነት

ክርስቶስ መጥቶ የክርስትናን አስተምህሮ የሰውን ልጅ መንፈሳዊ እሳቤዎች ከቀየረበት አብዮት በፊትም ቢሆን ስለ ትንሳኤ (ሕያውነት) ምንም ፍልስፍና አልነበረም ማለት አይቻልም። በግብጽ የኦስሪስ፣ በግሪክ አፈታሪክ የአኪሊስ እና ሄሪኩለስ እንዲሁም በሂንዱኢዝሙ ሳምባዶር ለዚህ ምሳሌ ሆነው መቅረብ የሚችሉ ናቸው።

ነገር ግን የሕያውነት ወይም ትንሳኤ ፍልስፍና ግልጽ ምስል መሰበክ የጀመረው በክርስቶስ ነው፤ በኋላም በእስልምና ሃይማኖት ተመሳሳይነት ያለው አስተምህሮ ተራምዷል። ይህም አስተምህሮ በምጽአት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው በራሱ ነፍስ ትንሳኤን ያገኛል፤ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሱ ታሪኮች ከሞቱ ኋላ የሚነሱ ሰዎች አሉ (ክርስቶስ ራሱ እና ክርስቶስ ያስነሳው አልአዛር)።

Resurrection የሚለው ቃል ከተመሳሳዩ ላቲን ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜው የሞተ ነገር ወደ ህይወት ሲመለስ ማለት ነው። ትንሳኤ ሁለት መገለጫዎች አሉት፤ መንፈሳዊ ትንሳኤና ቁስ አካላዊ ትንሳኤ። በመንፈሳዊ ትንሳኤ እይታ ማንኛውም ሰው ዘለዓለማዊት ነፍስ ስላለችው ከሞት ይነሳል፤ ዘለዓለማዊ ፍርዱን ይዞ ኑሮውን ይኖራል። በቁስ አካላዊ ትንሳኤ ደግሞ አንድ የሞተ ነገር ተመልሶ ሕያው ሲሆን ማለት ነው።

ነገር ግን ቁስ አካላዊ ትንሳኤ እንበል እንጅ የነፍስን ረቂቅነት እስከተቀበለ ድረስ የሐሳባዊያን ተቃራኒ የሆነውን ቁስ አካላዊ ፍልስፍና ማለታችን አይደለም። በዚህም ሁለቱም ዕይታዎች ተመሳስሎሽ ያለባቸው መሆኑን ልብ ማለት ይቻላል። ነገር ግን አንዳንዶች ደግሞ አይጠፉም፤ የሰው ልጅ የተሠራው ከቁስ ነው፤ ትንሳኤም ቢኖረው ቁሳዊ ትንሳኤ እንጅ ነፍስ የሚባል የለም የሚሉ አሉ።

በመካከለኛው ዘመን ፈላስፎች በተለይ በቅዱስ አውጉስቲንና ቅዱስ ቶማስ አኩይናንስ ይሄ አስተምህሮ ይበልጥ ተስፋፍቶና ፍልስፍናዊ ብያኔዎች እየተሰጡት ሲብራራ ችሏል። እንደ አኩይናንስ ዕይታ ሞት ለሰው ልጅ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን መሠረታዊም ነው፤ መሠረታዊነቱ ዘለዓለማዊ የሆነችው ነፍስ አዲስ ትንሳኤን ታይ ዘንድ ሞት ግድ መሆኑ ነውና። እንዲህም እያለ ይሞግታል፤ ነፍስ ከስጋ ውጭ መኖር ይቻላታል፤ ምክንያቱም ነፍስ በስጋ ውስጥ ትኖራለች እንጅ የስጋ ጥገኛ አይደለችምና።

ነፍስ በስጋ ውስጥ ስትኖር ይህን ዓለም መስላ ትኖራለች፤ እናም የስጋ ጥገኛ መስላ ትታያለች፤ እውነታው ግን ስጋ የነፍስ ጥገኛ እንጅ ነፍስ የስጋ ጥገኛ አይደለችም የሚለው የአኩይናንስ ፍልስፍና ነው። ስለዚህም ይላል አኩይናንስ ነፍስ ከስጋ ስትነጠል ይህን ዓለም የምታይበት መንገዱ ሌላ የኑሮ ዘይቤዋም ሌላ ይሆናል። አምፖል ቢሰበር መብራቱ ድርግም እንደሚለው ዓይነት አይደለም የስጋና ነፍስ መለዬት ለነፍስ ውጤቱ፤ ይልቁንም አዲስ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንደመብራት ዓይነት እንጅ። ይሁንና በትንሳኤ ጊዜ አምፖሉና ኤሌክትሪኩ ይገናኙና ያ ቀዳማዊው ሁነት (ዓለም) እንደገና ይታያል።

አውጉስቲን ደግሞ ያብራራው ነፍስ ኢመዋቲ መሆኗን አይደለም፤ ኢ-መዋቲ መሆን አለባት የሚለውን የፕሌቶን ፍልስፍና ነው። ነፍስ በተፈጥሮዋ ንጽህና፣ ብጽዕና፣ እና ፍጽምና የሚስማማት ናትና። ፕሌቶ ፍጹም ደስታ የነፍስ ጠባይ ነው እንዳለው አውጉስቲንም ለዚህ እውነተኛና ፍጹም ደስታ ደግሞ ሞት የሚስማማው ባህርይ አይደለም፤ እናም ነፍስ መዋቲ መሆን የለባትም፣ አይደለችምም።

ለአውጉስቲን ሞት ሁለት ዓይነቶች (ደረጃዎች) አሉት። የመጀመሪያው አንደኛ ሞት የሚለው የማትሞተው ነፍስ ከሚሞተው ስጋ ስትለይ ነው። እንዲህ ያለው ሞት የሰው ልጆች ሁሉ ባህርይ (እጣ ፈንታ) የሆነው አዳምና ሄዋን በሠሩት ሀጢአት ምክንያት ከአባቶቻችን በወረስነው መርገም የተነሳ ነው። ይህኛው ሞት የአምላክ ቅጣት ነውና በበጎ መታዬት አለበት ይላል አውጉስቲን። በጎነቱ ግን እንደ ቅጣት እንጅ እንደውስጣዊ ስሜት አይደለም። ውስጣዊ ስሜትን ያጤንን እንደሆነ ለበጎው

በጎ ለመጥፎው መጥፎ ውጤት ያለው ነው። በውጤቱ መልካም ከሆነ ነፍስን ወደቀጣዩ ጥሩ ሽግግር መግፍኤ ይሆናል።

ለአውጉስቲን ሁለተኛው የሞት ዓይነት ወይም ደረጃ ደግሞ የነፍስ መሞት ነው። እዚህ ላይ ነፍስ ኢ-መዋቲ ናት ከተባለ በኋላ የነፍስ መሞት እንዴት ይመጣል የሚለው ቁም ነገር መነሳት አለበት። አውጉስቲን እዚህ ጋ የ ነፍስ ሞት የሚለው እግዚአብሔር ነፍሳችንን በሀጢአታችን ሰበብነተ ሲርቃት ነው።

> It falls on us as a result of our own personal sin we commit in our life; and it is characterized by eternal damnation of our soul in the purgatory and then, when rejoin with the body, in hell; this death is good to none for it happen to nothing good (Augustine 1908: 3-4).

በእነዚህ እይታዎች መሠረትነት በሕያውነት (ትንሳኤ) ለሚያምኑ ሞት ዳግም እድል የላትም፤ አንድ ናት፤ ነፍስም ድጋሚ የምትፈጠርበት ዳግም እድል የላትም፤ አንዴ ዘላለማዊ ሆና ተፈጥራለች እንጅ።

## *ሞት መጨረሻ ነው*

ብዙ የሚባሉ ፈላስፎች ይህኛውን ፍልስፍና ያራምዳሉ፤ በዚህ ዓለም ውስጥ፣ በዚች ፍትሕ በጎደለባት፣ ደስታ በራቀባት ዓለም እየኖርን ነገ ሌላ ህይወት አለን እያልን ራሳችንን ማታለል ሳይሆን የመጨረሻ እና አንድ ህይወት ብቻ እንዳለን አውቀን የራሳችንን ህይወት ለማጣጣም እድሉ እጃችን ላይ ነው። የሰው ልጅ ሐሳቡ የማይገደብ ቢሆንም ቅሉ፤ ከዚህ የተሻገረ ዓለም እንዳለ ማሰብ የሚችልም ቢሆን እንኳ እውነታው አንዴ ከተሞተ በኋላ የሚያልቅ ነው ይላሉ እንደ ኢፒኩረስ (1940) ያሉ የዚህኛው ሐሳብ አራማጆች።

ይህ አስተሳሰብ ከጥንታዊያን ግሪኮች የአቶም ፍልስፍና እና ጥንታዊ ህንዶች ቻርቫካ ጀምሮ እስከዘመናዊያኑ ቁስአካላዊያን እና ኅሊዮአዊያን (ኤግዚስቴንሻሊስቶች) ድረስ ሲስተጋባ የኖረ ነው።

## *ቁሳካላዊ መሠረት*

ምንም የመጣው ከምንም ነው። ያ ምንም ደግሞ አተሞች አሉበት። ቁስ አካላት ከቁስ አካላት እንጅ ከአንዳች ሃይል (ፈጣሪ) የመጡ አይደሉም የሚለው ፍልስፍና ከጥንታዊ ግሪክ ፈላስፎች ጀምሮ የነበረ ነው። ነገሮች የመጡት ከአተም ነው ብሎ ከተነሳ በቁስ አካላዊ አስተሳሰብ መሠረት ሞት ማለት የመጨረሻ ማለት ነው፤ በሌላ አባባል ከሞት በኋላ የሚቀጥል ሕይወት የለም፤ አንድ ነገር ሞተ ማለት ፈረሰ፣ እንዳልነበር ሆነ ማለት ነው። ቁስ አካላዊያኑ እንደሚሉት ህይወት ማለት ስላለንበት ሁነትና ስለራሳችን ማወቅ ነው፤ መሞት ማለት ከዚህ ራስን ማወቅ ነጻ መሆን ሁነትንም ለመገንዘብ አለመቻል ነው። ከቁስ አካል የመጣን ነንና፤ ቁስ አካል ደግሞ በማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ ያለ ነው። በዚህም የተነሳ በየለውጡ አዳዲስ ፍጥረታት ይመጣሉ ይሄዳሉ፤ ሰውም ሲሞት ያበቃል፤ በሰው ስጋ ላይ የሚበቅል አበባ ደግሞ ይኖራል፤ ያን አበባ የሚቀስም ንብም።

ይህ ቁስ አካላዊ ፍልስፍና ቀስ እያለ በኤፒኩሪያን እና ሶቶይኪያን ፈላስፎች እየተላመደ በተለይ ምግባራዊ ፍልስፍናን ለማራመድ ሲያገለግል ቆይቷል። እዚህ ጋ የምግባር ፍልስፍና ሲባል የሰው ልጅ ሕይወት ምን መምሰል አለበት፣ እንዴት ያለ ህይወት ነው ትክክለኛ ሕይወት፣ ምን አይነት ዘይቤ ነው ጥሩ የኑሮ ዘይቤ፣ መጥፎስ? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እና በጊዜው በነበሩ ፖለቲካዊ ምስቀልቅሎሽ ተስፋ በማጣትና የህይወት ጣእምን ባለማወቅ ለሚባዝኑ ዜጎች መልስ ለማበጀት የተሄደበትን መንገድ ለመጠቆም ነው።

የሰው ልጅ ሊኖርበት የሚችለውን ፍልስፍና ይፈልጋል። እነዚህ ቁስ አካላዊያንም ይሄንን ለማሟላት የሞከሩ ይመስላል። ኢፒኩረስ ስለነገሮች አፈጣጠር (on the nature of things) በሚለው መጽሐፉ

እንደሚሞግተው ሞት ማለት የአተሞች መመሰቃቀል እንጅ ሌላ ማለት አይደለም። የአተሞች መመሰቃቀል በህይወት ቆሞ ይሄድ የነበረን ሰው ድጋሜ ቆሞ እንድናዬው አያስችለንም፤ ስለዚህም ሞት እንለዋል (J. Oates 1940:xxi)። ኢፒኩረስ ስለነፍስ መኖር ያምናል፤ ያ ነፍስ የሚለው ነገር ግን አንድ አተም እንጅ ሌላ አይደለም።

ሳይንስ በበለጸገበት ዘመናዊ ፍልስፍና ደግሞ ቁስ አካላዊነት ወደፊት እየገፋ አሸናፊ እየሆነ የመጣ የህይወት አተያይ (ፍልስፍና) የሆነ ይመስላል። ቁስ አካላዊነት በተለይ ፖለቲካዊ ካባ ለብሶ ዓለምን መሸከርከር የጀመረው ማርክሲዝም ካባን ለብሶ ነው። ምክንያቱም ካርል ማርክስ የሰው ልጅና ዓለም የመጨረሻ እውነታ ቁስ አካል መሆኑን በደማቁ አስምሮበት ነበር። የላይኛና የታችኛ ሥርዓቶች ወይም መደቦች ብሎ ማርክስ ያስቀመጣቸው የሐሳብና የቁስ ምድቦች በቀጥታም በተዘዋዋሪ ቁስ አካላዊ ናቸው። የላይኛው መደብ ሐሳብ ነው፤ ይህ ሐሳብ ግን ምንም ማለት አይደለም፤ የቁስ አደራደር ጥበብ እንጅ።

ስለሞት ያላቸው እሳቤም ቁስአካላዊ እውነታን የተከተለ ነው። ማርክሲስም በተፈጥሮ ዲያሌክቲክና በታሪክ ዲያሌክቲክ (የለውጥ እጥፋቶች) ላይ የሚንጠለጠል እንደመሆኑ ሞትም በዚሁ እምነታቸው ላይ የተንጠለጠለ ነው።

## *ኅልዮአዊ (Existential) ሐተታ*

የዚህ ፍልስፍና ልብ (ማዕከል) ኅልዮ ከሥሪት ይቀድማል (existence proceed essence) የሚል ነው። ኅልዮአዊያን እንደሚሉት ከምንም እንሠራ፣ መቼም እንሠራ፣ ማንም ይሥራን እነዚህ ጥያቄዎች ሁለተኛ ደረጃ ላይ መምጣት ያለባቸው ናቸው። ከሁሉ በፊት ኅልውነት እና ኅልዮ ላይ ነው ማውራት ያለብን ይላሉ።

የዚህ ፍልስፍና አራማጅና በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑቱ እንዲህ ይላሉ፤ ብቻችንን ነን፤ ዶስቶቭስኪ በየስርቻው መጣጥፍ ውስጥ እንደሳለው ገጸ ባሕርይ ሁሉ ለኅልዮ ጥያቄዎቻችን ምላሽ ማበጀት ያለብን እኛ እንጅ ማንም አይደለም፤ እግዚአብሔር ይሞላልናል የሚባል ቦታ የለንም፤ ራሳችን እንጅ ይላሉ። እጣ ፈንታችን በእጃችን ነው ይላሉ፣ ከእነዚህ ወገን የሆነው ኒቼ ይህን amore fete ሲል ይጠራዋል። እጣ ፈንታህን ውደድ እንደማለት። (Barry 1980:54-56).

አንዳንድ ኅልዮአዊያን ሞትን እንደተራ የሕይወት አደናቃፊ ይመለከቱታል። ሞት ህይወትን የሚረብሽ (የሚያደናቅፍ) ተራ ነገር ነው። እነሱ እንደሚሉት ሞትን ከእንቅልፍ የሚለዬው ቋሚ መሆኑ እና እንደእንቅልፍ በአጭር ጊዜ የማይጠናቀቅ መሆኑ ነው። ስለሆነም ሞት ወደሌላ ሁነት ልንሸጋገርበት የምንችል ሳይሆን የህይወት ፕሮጀክት ፍጻሜ ነው ይላሉ። ኒቼ የዚህ መድሃኒቱ አሁንን መኖር ነው፤ ኑሮን ማጣጣም እና መሥራት ነው ይላል፤ አልበርት ካሙ (Camus, 1955). ደግሞ እምቢታ ነው ይላል። (እምቢታው ለሥርዓቶች ነው) ሃይዲገር ደግሞ ሞት የህይወት አካል ነው ይላል፤ እንደመጣነው እንሄዳለን፤ እናልፋለን፤ የሕይወት አካል የሆነው ሞት ሲመጣ እኛ (በህይወት) የለንም። ስለዚህም ሞት በኅልዮ ውስጥ የሆነ ጊዜ ላይ የሚመጣ እውነታ ነው። (Couzens 2009:282-284)

በጠቅላላው የኅልዮ ፍልስፍና አራማጆች ሕይወት አንድ ጊዜ የምንኖረው ነው ይላሉ። ከሞት በኋላ ህይወት አለ የሚለው የሰው ልጅ የማያርፍ አእምሮ የፈጠረው፣ ለህይወት ትርጉም በሚፈልግ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ሄዶ ከዚህ ዓለም ሌላ የመኖሪያ ዓለም ብሎ የፈጠረው እንጅ በህይወት ውስጥ አንዴ ሞት ከመጣ ነገሮች እዚያ ጋ ያቆማሉ የሚል ፍልስፍናን ያራምዳሉ።

## ትንታኔ

በዚህ ክፍል የተመረጡት አራት ግጥሞች ይዘታቸውን ሊያሳይ በሚችል መልኩ እየተቀነጨቡ ይቀርባሉ። በውስጣቸው ያለው ፍልስፍናዊ እይታ ይተነተናል። ገጣሚዎቹ የሚወግኑባቸው የሞት ፍልስፍናዎች ይጠቆማሉ።

## አንድ ፀሐይ (አንዷለም አባተ)

ከተመረጡት አጭሩ ግጥም የአንዷለም አባተ ‹አንድ ፀሐይ› ነው፡፡ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኀበር በ1999 ዓ.ም ባሳተመው ‹የዘመን ቀለማት› በተባለ መድብል ውስጥ የተካተተ ይሁን እንጅ ገጣሚው በ2000 ዓ.ም የረዘመ ትንፋሽ በሚል ርዕስ ስር ባሳተመው የግጥም መድበልም የተካተተ ግጥም ነው፡፡

… ቢስ እያየብኝ የሎስ እያንጃበበ
በልቤ መቃብር እቆፍራለሁ
ልቤን ምሼ
ልቤ አፈር ውስጥ ሰውን ያክል እቀብራለሁ
ከዋክብቴን እቀብራለሁ
ሻማዎቼን እቀብራለሁ
ዛሬ ግን ልቤ ላዘን ጠበበ
እንባ ጅረቱም ወግ አጣ
ዛሬ ግን ከጨረቃም የላቀ
ዛሬ ግን ከእልፍ ከዋከብት የደመቀ
ዛሬ ግን አንድ ፀሐይ ቢኖር ጠለቀ

በ1998 ዓ.ም እንደጻፈው ገጣሚው ማስታወሻውን አስቀምጧል፡፡ ከላይ ያልተጠቀሱት ስንኞች - ገጣሚው ከዚህ ቀደም ከዋከብት ሲረግፉ ያለቅስ እንደነበር፣ ሻማዎች ሲጠፉ ያለቅስ እንደነበር፤ ለዚህ ሁሉ ሀዘን የልቡን በልቡ ይይዝ እንደነበር ይገልጽና ፀሐይ በመጥለቋ ግን - አሁን ኀዘንኑን መሸከም የሚችል ስፍራ ከውስጡ እንዳጣ ይናገራል፡፡

ጸጋዬን ከፀሐይ ጋር ነው የመሰለው፡፡ አሁን ፀሐይ ጠለቀች ነው ያለው፡፡ ከጨረቃ የላቀ ከእልፍ ከዋከብት የደመቀ ይለዋል፡፡ ሳይንስን ማነጻጸሪያ አድርገን ብናዬው ጨረቃና ከዋከብት ብርሃናቸውን ከፀሐይ ያገኛሉ፡፡ ፀሐይ ከሌለች ብርሃናማ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በዚህ መንገድ ጸጋዬ ብርሃን ሰጭ ሆኖ ተሥሏል፡፡ ይሁንና የጸጋዬ ተምሳሌት እንዴት ነበር? የወረቀቱ ትኩረት አይደለምና አንዷለም የትኛውን የሞት ፍልስፍና አራመደ ወደሚለው እንሂድ፡፡

ለአንዷለም ሞት ግልጽ አይደለም፡፡ ሞት የመጨረሻ ነውን? ይሄን ጥያቄ ለአንዷለም ወይም ለግጥሙ ብናቀርብ ቅልብጭ ያለ መልስ ልናገኝ የምንችል አይመስልም፡፡ ‹ፀሐይ ጠለቀ› ነው ያለን አንዷለም፡፡ በተምሳሌቱ ከሆነ ፀሐይ ማታ ብትጠልቅም ጠዋት ተመልሳ ትወጣለች፡፡ ስለዚህ ሞት የመጨረሻ አይደለም ማለት ነው ለአንዷለም፡፡ ነገር ግን ከላይ በጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፋችን ውስጥ ለማዬት እንደሞከርነው ሞት የመጨረሻ አይደለም ብለው የሚያምኑቱ በሁለት ጎራዎች ይቆማሉ፡፡

አንደኛው ነፍስ አሁን ያለችበትን ስጋ ከለቀቀች (ሞት ከተከሰተ) በኂላ እንደ ጽድቅ መጠኗ በሌላ ህይወት ያለው ፍጡር በኩል ትመጣለች፡፡ በፍልስፍናው አራማጆች እንደሚባለው ደስተኛ (መልካም) ነፍስ በንጹሃን እንስሶች ወይም ተክሎች በኩል ትመጣለች፡፡ መልካም ያልነበረች ነፍስ ከሆነች፣ ሐጢአተኛ ነፍስ የሆነች እንደሆነ ደግሞ መከራ በሚበዛባቸው እንስሳት (እንደጭነት እንስሳት) ባሉት ስጋ ዳግም ትመጣለች፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ነፍስ ዘለዓለማዊት በመሆኗ ከስጋ ተለዬች ማለት አለቀላት ማለት እንዳልሆነ የሚፈላሰፉበት ነው፡፡ በዚህኛው ፍልስፍና አተያይ ሞት ማለት የነፍስና ስጋ መለያየት ነው፤ ስጋ ቀሪ፣ ፈራሽ እና በስባሽ ነው፤ ነፍስ ደግሞ ዘለዓለማዊት በመሆኗ ወደ ሰማይ ታቀናለች፤ በዚያም የዘለዓለም ህይወትን ትጀምራለች፡፡ በእርግጥ በትንሳኤ ጊዜ ስጋና ነፍስ ተመልሰው ይገናኛሉ፡፡ ያው የነበረው የድሮው ስጋ እንጅ አዲስ ስጋ አይፈጠርም፡፡

በሁለቱ ምልከታዎች መነሻ ነጥቦችን ወስደን የአንዷለምን ፍልፍናዊ መዳረሻ ስንመለከት ማረፍያ እናጣለን፡፡ ጸጋዬን ፀሐይ ነው አለው፤ ፀሐይ ስለሆነ ጠለቀ፤ ስለጠለቀ እና ፀሐይ ስለሆነ ሲነጋ ተመልሶ እንደሚወጣ እናምናለን፡፡ ነገር ግን ጠዋት ሲወጣ በምን መልኩ ነው ተመልሶ የሚወጣው የሚለው አንዷለም ግልጽ አቋም አላስቀመጠም፡፡

ጠዋት ሲወጣ በአዲስ ሥጋ፣ በአዲስ አይነት ፍጥረት ነው የሚወጣው ወይስ በራሱ በጸጋዬ ሥጋ? በአዲስ ሥጋ ደግሞ ደግሞ የሚመጣ ከሆነ (ፀሐይ ዕለት እለት እንደምትወጣው) ራሱ ጸጋዬን ማግኘት እንችላለን? ወይስ በዕየለቱ አዳዲስ ፍጥረት? እንዲያ ከሆነ ጸጋዬን ዳግም አናገኘውም ማለት ነዋ! ኦሮሚኛ፣ አማርኛ፣ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ላይ የሚራቀቀውን ጸጋዬን አንዴ ተሰናብተነዋል፤ ድጋሜ አናዬውም፡፡

ጸጋዬን በየእለቱ በጸጋዬ ሥጋ ከሆነ የምናገኘው ደግሞ ጸጋዬ አንቀላፋ እንጅ ሞተ ልንል አንችልም፡፡ በዚህ ዕይታ ከሄድን ደግሞ አንዷለም ሞትን እንደ እንቅልፍ አድርጎ ይመለከተዋል ለማለት ላንችል ነው?

ነገር ግን የአንዷለምን ፍልስፍና ስንወስድ ሞት የመጨረሻ አይደለም፤ ቀጣይ ህይወት አለ የሚለውን መከራከሪያ እንደሚያራምድ እንመለከታለን፡፡ እንግዲህ የአንዷለም የሞት ፍልስፍና ሞት የመጨረሻ አይደለም የሚል ከሆነ ስለምን ጸጋዬን በፀሐይ ሲመስል፣ ሌሎች ከእሱ ቀደም የሞቱትን በከዋከብት እና በሻማ መሰላቸው? ከዋከብት ፀሐይ እስካለች መኖር ይችላሉ፤ ሻማ ግን የፀሐይ መኖርና አለመኖር የሚፈይድለት ነገር የለውም፡፡ ወዲያውም ሻማ አልቆ ከጠፋ ዳግም ሊገኝ የሚችል አይደለም፤ ሌላ ሻማ እንለኩስ ካልሆነ በቀር ያ የቀደመው ሻማ ቀልጧል፤ ጠፍቷል፡፡

የአንዷለምን መከራከሪያ ስናይ ሞት የመጨረሻ አይደለም ወደ ሚለው አተያይ ወስደናል፤ ነገር ግን እዚህ ጋ ደግሞ ሌላ አቋም ያለው ይመስለናል፡፡ ለክርክር እንዲያግዘን ጥቂት ሀረግ እንጥቀስ *‹‹የተለኮሱ ረጃጅም ሻማዎች ሲጠፉ የሀዘን ጋቢ አጣፍቼ ከእዬየ ጋር እባጃለሁ››* ‹ረጃጅም› የሚለው ገላጭ ሻማዎቹ አልቀው ቀልጠው የሚጠፉት እንዳልሆኑ ለማመልከት ይመስላል፡፡ መልሰው መልሰው ሊለኮሱ የሚችሉትን ለማለት ይመስላል፡፡ እንዲህ ከሆነ እላይ ያየነው የአንዷለም የሞት ፍልስፍና አንድ ደርዝ ያለውና የማይናወጥ ነው ለማለት እችላለን፡፡ ሻማ ከጠፋ ዳግም ይለኮሳል (በአንድ ሌላ ኃይል ላይ የተንጠለጠለ ብርሃን አለው) ጨረቃ ዛሬ ከጠለቀች ነገ ትወጣለች (በአንድ ኃይል ላይ የተንጠለጠለ ብርሃን አለው) ከዋከብት ዛሬ ከጠፉ ነገ ይወጣሉ (በአንድ ኃይል ላይ የተንጠለጠለ ብርሃን አላቸው) ፀሐይ ዛሬ ከጠለቀች ነገ ደግሞ ትወጣለች (በአንድ ኃይል ላይ የተንጠለጠለ ብርሃን አላት) ይህ ትናንት የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ያ ኃይል እስካለ ድረስ (እስካሁን መኖሩን እንጅ አለመኖሩን ማረጋገጥ ስላልተቻል) ሃይሉ እስካለ ይህ ዑደት ይቀጥላል፡፡ ስለዚህም ሰው ይወለዳል፤ ሰው ይሞታል፤ ነገር ግን ሞቶ አይቀርም፡፡ ደግሞ ይወለዳል፡፡ ሞት የመጨረሻ አይደለምና፡፡ የአንዷለም ፍልስፍና ሞት የመጨረሻ አይደለም የሚለው በኢንዳክሽን ትወራ ሊረጋገጥ ችሏል፡፡ ነገር ግን የመጨረሻ አይደለም ይበል እንጅ ከዚያ የሚቀጥለው ምንድን ነው? የነፍስ ቅርጽ (state) እንዴት ያለ ነው ለሚለው መልስ የለውም፡፡

## ‹ሞተ እኮ› የሚለው ይሙት (ፀሐይ መላኩ)

ረዘም ያለ ግጥም ነው፡፡ መቼ እንደተጻፈ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን መጽሐፉ 1999 የታተመ ጸጋዬም 1998 ያረፈ መሆኑ ይታወቃልና ከሁለት በአንዳቸው ዘመን እንደተጻፈ መገመት ይቻላል፡፡ ለትንታኔ ከተመረጡ ግጥሞች ውስጥ እንዲሆን ያስቻለው የገጣሚዋን የሞት ፍልስፍና ማሳዬት የሚችል ግጥም በመሆኑ ነው፡፡

ተፈጥሮ ውሏን አትረሳ
ህይወትን ከሞት ማድራቷን ማቅመሷን አትዘነጋ
የደስታ የሀዘን ግቷን ይችው ጉድ ይችው አዚማም ቀን ቆጥራ
ዘመን ቀምራ አስልታ ይዛው ነጎደች ኃያሉን የጥበብ አውራ
መለዬት ጽልመት ቢውጠን ባዶነት ቢያንቀጠቅጠን
እጦቱ ምን ቢቧጥን ጸጋዬ ጸጋችን አርፏል እንግዲህ ጥናቱን ይስጠን!

በግጥሙ ውስጥ ያሉ ፍልስፍናዊ አገላለጾችን እንይ፡፡ አስቀድሞ ተፈጥሮ ውሏን አትረሳ ህይወትን ከሞት ማድራቷን ይላል፡፡ ተፈጥሮ በአንድ ሊቀየር በማይችል ህግ የምትተዳደር መሆኗን ያጠይቃል፡፡ ይህ ሊቀየር የማይችል ህግ ደግሞ ህይወት ከሞት ጋር ሞትም ከህይወት ጋር አብረው የሚኖሩ መሆናቸው፡፡

በግጥሙ ውስጥ ‹አስልታ ይዛው ነጎደች ሃያሉን የጥበብ አውራ› የሚል ሀረግ ይገኛል፡፡ በዚህ ሀረግ የተገለጸው ነገር የጸጋዬ በህይወት መለየት ነው፡፡ ነገር ግን ጸጋዬ በሕይወት ተለዬ ሳይሆን የተባለው ሞት ጸጋዬን ወሰደው ነው፤ ወሰደው ብቻ አይደለም፤ ይዞት ነጎደ እንጅ፡፡ ‹ነጎደ› የሚለው ቃል አለመመለስን የሚያመለክት ነው፡፡ ‹‹ነጎደ›› .... ጭልጥ ብሎ በመንገድ ሽምጥጦ ሄደ፣ መለስ ቀለስ አላለም፣ (ከሳቴ ብርሃን ተሰማ 1921፡674)

መለዬት ጽልመት ቢውጠን እና ባዶነት ቢያንቀጠቅጠን የሚሉ ሀረጋትም በግጥሙ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሀረጋት ሲዘጋም ጸጋዬ ጸጋችን አርፏል እንግዲህ ጥናቱን ይስጠን! በሚል ሀረግ ነው፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ ሞታዊ ፍልስፍና አለን የሚያሰኙን እነዚህ ሀረጋት ናቸው፡፡ ገጣሚዋ ፍልስፍና የት ጋ ይወድቃል?

በጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፋችን ለማዬት እንደሞከርነው ኃልዮአዊ (ኤግዚስቴንሻሊስት) ፈላስፎች ሞት የህይወት አካል ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሞት የሚባለው ነገር አይቀሬ እና በሆነ አጋጣሚ የሚመጣ ነው ይላሉ፡፡ ለምሳሌ ኒቼ የዚህ መድኃኒቱ አሁንን መኖር ነው፤ ኑሮን ማጣጣም እና መሥራት ነው ይላል፤ አልበርት ካሙ ደግሞ እምቢታ ነው ይላል፡፡ ሃይዲገር ደግሞ ሞት የህይወት አካል ማለታቸውን አይተናል፡፡

በፀሐይም አመለካከት ሞት የህይወት አንዱ ገጽ ብቻ ሳይሆን ህይወትን የሚያደናቅፍ ነገር ነው፡፡ ስለዚያ ነው ‹ይች አዚማም ቀን አስልታ ዘመን ቆጥራ› እያለች የምትብሰከሰከው፡፡ እነ ኒቼ እንደሚሉትም ለኃልዮአዊ ሞት ፍልስፍና አራማጆች ሞት መቼም ሊመጣ የሚችል በመሆኑ፤ ከዚያ በኋላ የሚቀጥል ህይወት ባለመኖሩ ህይወታችንን ዛሬ እና አሁን እዚህ ጋ መስራት ያለብን እኛ ነን ይላሉ፡፡ ፀሐይም ይህንን አቋም ታራምዳለች፤ እንዲህ እያለች፡-

እንጠይቅ እኛም ይድረሰን እድሉ ገዱ ትቀፈን
ጸጋዬ ጸጋው ይትረፈን ሰርቶብን ጊዜ እንዳያልፈን
ይበለን እነሆ ጀባ አዱኛ ፍቅሩን ያልብሰን
ይስረጸን ታማኝነቱ ጽናቱ ሀቁ ያውርሰን

የፀሐይ መላኩ ሞታዊ ፍልስፍና ኃልዮአዊነት የተላበሰ ነው፡፡ ነገ የሚቀጥለውን ህይወት ራሳችን የሠራነው ምናብ ነው፤ ዛሬ፣ እዚህ ጋ ነው የእኛ ሕይወት ያለው፡፡ ይህንን ህይወት መሥራት ማጣጣምና እንደሚገባው መኖር ነው የእኛ ድርሻ፤ ከሄድንማ እንደጸጋዬ በቃ መለዬት ነው፤ መተጣጣት ነው፤ መገናኘት የለም ትላለች፡፡ ስለዚህም እንደጸጋዬ መሥራት፣ በተሰጥኦ ትሩፋታችን ኑሯችንን ማቃናት እንጅ በሌላኛው ዓለም የሚል መግለጫ አሳማኝ አይደለም እያለች ትፈላሰፋለች፡፡

## ለካ ሞት ግጥም አይችልም (ነቢይ መኮንን)

በ1998 ዓ.ም የካቲት ወር የተጻፈ ግጥም ነው፡፡ በመጽሐፍ የታተመው ደግሞ በቁጥር 2 ሥውር ስፌት በ2006 ዓ.ም ነው፡፡ ግጥሙ ሁለት ገጽ የያዘ ነው፡፡ አገማመዱ፣ አወራረዱ፣ መከራከሪያውና ማሳያው ፍልስፍና ነው፤ የነቢይን ግጥምና ፍልስፍና አጣምሮ ያያዘ ግጥም ነው፡፡

እኔ ገጣሚው ልቅሶ ቤት
ልቤን ላነባ ስገባ
ሞትም ተከትሎኝ ገባ
እኔ ወዲህ ማዶ ቆምሁኝ
እሱ ወዲያ ማዶ ቆመ
ከመሃል ገጣሚው አለ

ገጣሚው የፊደል አርበኛ አይደለ አስክሬኑ ጃኖ ለብሷል
ስደተኛ ወንዝ አይደለ
ወንዝ አለት እንደሚንተራስ ብረት ሳጥን ተንተርሷል …

በእርግጥ በጌትነት እንየው ‹ባዶዬን መጣሁኝ› ግጥም ውስጥም ሞትን እንደ ገጸ ባህርይ ተመስሎ ይገኛል። ነብይም ሞትን፣ ሚችን እና አዛኝን በሦስትነት አብሮ አቁሞ ነው የሚያሚግታቸው። ይህ ገጣሚው በፍልስፍና እና ግጥም ሙያ ጋብቻ ላይ ያለ ሆኖ እንዲሰማኝ አድርጓል።

… ሞት ለዘለዓለም ይኑር
የሚል ሽቃባ መፈክር እርኩስ ደረትህ ላይ ጽፈህ
ግጥም መማር ታስባለህ?
ግጥም የሕያው ልሳን ነው ለሞት አንደበት አይሆንም
የስንኝ ጠበል እሚፈልቅ በድን አለት ውስጥ አይደለም
ግጥም ከነብስ ቃል እንጅ ከሥጋ ትንፋሽ አይነጥብም
አንዳች ህይወት ውስጥህ ሳይኖር ፊደል በመቁጠር አትገጥምም

የነብይ ፍልስፍና ወደ ፕላቶኒክ አተያይ ያደላ ይመስላል። የፐሌቶን የፍልስፍና አምዶች መሠረት ያደረገው ፕላቶኒክ አተያይ ነፍስና ስጋ ልዩ ልዩ መሆናቸውን ያምናል። ጥበብ በሥጋ ውስጥ ቢኖርም እውነተኛ ጥበብ ግን በነፍስ ውስጥ ያለና ዘለዓለማዊ ነው። እውነተኛው እውነትና የእውነቱ ነጸብራቅ የሚለው ነው ፐሌቶ።

ቆንጆ ሴት የእውነት ነጸብራቅ ናት - ቁንጅና ደግሞ እውነት።
ፊደል መቁጠር ነጸብራቅ ነው፤ ግጥምን ማወቅ ደግሞ እውነት
ቆንጆ ሴት ሥጋ - ቁንጅና ደግሞ ነፍስ
ፊደል ማወቅ ሥጋ - ግጥም ደግሞ ነፍስ
ሥጋ ሙት ልሳን - ነፍስ ደግሞ ሕያው ልሳን
በድን የህይወት ነጸብራቅ - ነፍስ ደግሞ እውነተኛ ህይወት
ሞት ነጸብራቅ ህይወት ደግሞ እውነት

ከፐሌቶ ዲበአካላዊ ትወራ ተነስተን ስንተነትን የምናገኘው ይህን እውነታ ነው። ይህ እውነታ ደግሞ በነቢይ ፍልስፍና ውስጥ የተገኘም ፍልስፍና ነው። ስለዚህም የነቢይ ሞታዊ ፍልስፍና ነፍስ ኢ-መዋቲ ናት። ይህች ኢ- መዋቲ የሆነች ነፍስ ደግሞ ሚች በሆነ ሥጋ ውስጥ ትኖራለች፤ ነገር ግን ባህርያቸው ለየቅል ነው፤ የሥጋ ባህርይ ነጸብራቅነት የነፍስ ባህርይ እውነትነት ነው።

ይህን ሰምቶ መልስ ሲያጣ
ሞት የሚባለው ፈጣጣ
ጭራውን ሸጉቦ ወጣ!

ይላል ነቢይ የሥጋን እና የነፍስን ልዩ ልዩነት ሲናገር። ሞት ሥጋ ነው፣ ነፍስ ህይወት ናት። ለፐሌቶ ሞት ማለት የነፍስና ሥጋ መለያየት ነው፤ መለያየቱ እርግጥ ሲሆን ነፍስ ከሥጋ ተላቃ በራሷ ሕያው ትሆናለች፤ ከሥጋ ተጽዕኖ ነጻ የሆነችው ነፍስም በራሷ የምትቆም ትሆናለች። ሥጋ ግን እንዲሁ ይቀራል። ይበሰብሳል፤ ይፈርሳል። ነቢይ እዚህ ድረስ ፕላቶኒክ የሞት ፍልስፍና አራማጅ ነው። ነገር ግን ለፐሌቶ እያንዳንዱ ነገር ሁለት አጣማጆች አሉት፤ አንደኛው ብልሽት (መጥፎ) እና መሠሪያ አላባ (መልካምነት)። በመሆኑም በነፍስ ብልሽት ማለትም ግድ የለሽነት፣ ጨካኝነት፣ ጋጠ ወጥነት በመሳሰሉት የምትበላሽ ናት፤ ይህ ብልሽት ነፍስን የማትረጋ እና እርካታ የለሽ ያደርጋታል እንጅ ጨርሶ የሚያጠፋት ነገር አይደለም። (1989:37)

እዚህ ላይ ጥርት ያለ ምስል በነቢይ ፍልስፍና ውስጥ አልተገኘም። በእርግጥ የጸጋዬ ነፍስ የተሳለበት መንገድ ፐሌቶ መልካም ነፍስ በሚለው መንገድ ነው። ለፐሌቶ መልካም ነፍስ ማለት ፍልስፍናን፣ እውቀትን እና ጥበብን የተጠማች፣ ለመማርና ለፍትህ የታተረች፣ መልካም ትሩፋትን የሠራች ናት። ይህች ነፍስ እውነተኛ ደስታን ታያለች፣ መልካም ህይወትንም ታጣጥማለች።

ስንፍና የተጠናወታት ነፍስ፣ መፈላሰፍን ያልወደደች፣ መብልን ብቻ ያዘወተረች እና ክፉ ነፍስ ደግሞ ትቃትታለች፤ መቅበዝበዝን እንጅ እውነተኛ ደስታን በሌላኛው (እውነተኛው ዓለም) (የፕሌቶ ሐሳባዊ ዓለም ወይም ዩቶፒያ) ውስጥ ለማዬት የምትችል አትሆንም።

ነቢይ በግጥሙ ከፕሌቶ ጋር የተመሳሰለ ፍልስፍናን ካሳዬን በኋላ የነፍስ መጨረሻዋ ምንድን ነው ለሚለው የሰጠን ምላሽ የለም። ነፍስስ ምን እጣ ፈንታ ይኖራታል ለሚለው እንደፕሌቶ አብራርቶ አልነገረንም።

ሌላኛው ልዩነት ደግሞ በፕሌቶ ፍልስፍና ውስጥ ነፍስ እውነተኛ ኑሮዋን የምትኖረው በራሱ በፕሌቶ ሐሳባዊ እውነተኛ ዓለም ውስጥ ነው። ሥጋ ደግሞ እውነት ሳይሆን የእውነት ነጸብራቅ በሆነው ዓለም ነው እጣ ፈንታው። ነቢይ እዚህ ላይ ግልጽ ፍልስፍና የለውም። ያች የጸጋዬ ነፍስ መኖሪያዋ የት ይሆን? የመገኛ ቅርጽዋ (state) ምን አይነት ነው? ለዚህ የሰጠን ምላሽ የለም። ነገር ግን በነቢይ ግጥም ውስጥ ግጥም ከፍልስፍና ተጋብታለች ብሎ መደምደም ይቻላል።

## ለአባታለም ጸጋዬ (አበባው መላኩ)

ግጥሙ መቼ እንደተጻፈ የሚገልጽ ነገር የለም፤ ነገር ግን ገጣሚው በ2000 ዓ.ም ባሳተመው የግጥም ሲዲ ግጥሙን አካቶታል፤ በመጽሐፍ ደግሞ በ2007 ዓ፣ም ‹እኔ ነኝ› በሚለው መጽሐፉ አንድ ግጥም ሆኖ ቀርቧል። የዚህኛው ገጣሚ ሞታዊ ፍልስፍና ሞት መጨረሻ አይደለም በሚለው ጎራ ውስጥ የሚወድቅ ሆኖ በነፍስ ሕያውነት (ትንሳኤ) የሚያምን ዓይነት ነው።

ስማኝ ልንገርህ አባት አለም በነፍስህ እዝነ ልቡና  
የአካል ቁራጭ እትብትህ ከተቀበረበት ደብር ከአባት ከእናትህ ከተማ  
በእግረ ስጋ ከኖርክበት የቅኔ አዝመራን አሽተህ እንበለ ድካም ወጻማ

በዚህ ግጥም ውስጥ ያሉ ቃላትን ስንመለከት ከላይ የተነሳንበት ቢሆን (ፕሪሚሰስ) ልክ ወደሚሆንበት መደምደሚያ የሚያደርሰን ይመስላል። ‹በነፍስህ እዝነ ልቡና› ‹እትብትህ ከተቀበረበት› ‹በእግረ ሥጋ ከኖርክበት› የሚሉ ገላጮች አሉ።

ይህም ግጥሙ የሚጻፍለት ጸጋዬ ተወልዶ፣ በሥራ ላይ ኖሮ ነፍስ ወደምትቀመጥበት ስፍራ ማምራቱን የሚገልጽ ትረካ ነው። ይህ የትረካ መንገድ ነፍስ ኢ-መዋቲ ናት፣ በትንሳኤም ዳግም ትነሳለች፤ ያኔም ፍርዷን አግኝታ ዘለዓለማዊ ኑሮዋን ትመሠርታለች የሚለውን የሞት ፍልስፍና የሚመስል ነው።

በየቀኑ ሙት አልልህ ነገር አብዬ አንተ ሆንክብኝ  
ደፋር ብዕርህ ይባረክ ነፍስህን ቢስ አይይብኝ

የሚሉት ሀረጋትም ገጣሚው አበባው መላኩ የተከተለው ፍልስፍና የትኛው እንደሆነ ለመረዳት የሚያግዙ ናቸው። የትንሳኤ ህይወትን ያስተማረው ክርስቶስ ‹ሙታንን ለሙታን ተዋቸው› ሲል የተናገረበት ክፍል እዚህ ጋ የሚሰምር ይመስላል። በየቀኑ የሚሞቱ፣ ከትንሳኤ ህይወት ጸጋዎች መካፈል የማይችሉ ድኩማን ይሄን ዓለም ሞልተውታልና! አበባውም በየእለቱ ሙት አልልህ ነገር ሲል የትንሳኤ ህይወትን ጸጋዎች ተቋደስ ማለቱ ይመስላል። ቀጥሎም ነፍስህን ቢስ አይይብኝ ይላል። ነፍስህ ከዳግም ህይወት (ከትንሳኤ) ጸጋዎች ተቋዳሽ ትሁን፣ ምቀኛ አይተናኮላት፣ ክፉዎች አይተንኩሉባት ለማለት ይመስላል። በቀጥታም በተዘዋወሪ በእስልምና ወይም ክርስትና እምነቶች አስተምህሮ ስለ ትንሳኤ መረጃዎች ስለሚኖሩ ከዚህ በላይ ማስፋቱ ጥቅሙ እምብዛም ነው።

## ማጠቃለያ

የግጥም እና የፍልስፍና በተለይም የሞት ፍልስፍና ሙያዎች ጥምረትን ለማዬት የሞከርኩበት ወረቀት ይሄው ነው። አራት ገጣሚዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የጻፏቸውን ግጥሞች በመመልከት የተፈላሰፉባቸውን መንገዶች ለማሳየት ሞክሬያለሁ። ገጣሚዎቹ በሥራዎቻቸው ውስጥ ሲታዩ

እንደሚችሉት ሞትን በልዩ ልዩ አረዳድ ተመልክተውታል፡፡ ምንም እንኳ የመጨረሻ መደምደሚያው ከሁለቱ ታላላቅ የሞት ፍልስፍናዎች ማለትም ‹‹ሞት የሰው ልጅ የመጨረሻ ነው›› እና ‹‹ከሞት በኋላ አዲስ ህይወት›› በሚሉት ጥቅል ምልክታዎች ሥር የሚያርፉ ቢሆንም ቅሉ አራቱም ገጣሚያን የየራሳቸው የሆኑ አረዳዶችን በግጥሞቻቸው ማሳዬት ችለዋል፡፡ ሞት ለአበባው መላኩ ነፍስ ወደ ተቀደሰ ቦታ የምትወሰድበት ሲሆን ለነቢይ ደግሞ መልካም እና መጥፎ ነፍሳት የሚለዩበት ሁነት ነው፡፡ ሞት ለፀሐይ ደግሞ ወደ አዲስ ዓይነት ዓለም የምንሸጋገርበት አይደለም፤ ሰው ነገ ወደ ሌላ ዓለም እንሄዳለን በማለት ስንፍና ሳይሆን ዛሬ ራሱን እየሠራንበት ልንኖር የሚገባ ነው ትላለች፡፡ አንዷለም ደግሞ ሞት የህይወት ዑደት ሰንሰለት መሆኑን ያምናል፤ ነገር ግን ከሞት ወዲያ ነፍስ ወዴት ናት ለሚለው የሚሰጠው ምላሽ የለውም፡፡

በጠቅላላው በዚህ ወረቀት አራቱ ገጣሚያን ሞትን እንዴት እንደሚመለከቱት ለማሳዬት እንደተሞከረ አምናለሁ፡፡ ከዚህ በሰፋ መንገድ ለማዬት ለሚፈልጉ ጥሩ መግቢያ መሆን የሚችል ጥናት ነውም ብዬ አስባለሁ፡፡

## ማጣቀሻዎች


ተሰማ ሀብተሚካኤል ግጽው።1951።*ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፤ ጎልደን አሳታሚ አርቲስቲክ ማተሚያ

የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር። 1999። የዘመን ቀለማት፣ *‹ሞተ እኮ› የሚለው ይሙት።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት

የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር። 1999። *አንድ ፀሐይ፡፡* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጀት

ነቢይ መኮንን፡፡ 2006፡፡ *ሥውር ስፌት*፡፡አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ማተሚያ ድርጅት

አበባው መላኩ። 2006። *እኔ ነኝ።*አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ማተሚያ ድርጅት

ጸጋዬ ገብረ መድኅን (ተርጓሚ) ፡፡ 1964፡፡ *ሃምሌት፡፡* አዲስ አበባ፤ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ

Augustine S. 1968. *The city of God,* VII, John Healey (trans.). London: Aldine Press

Barry V. 1980. *Philosophy: a text with readings*. California: wads worth press.

Benjamin J. 1989. Great books of western world: Plato*, "Phaedo", Hutchins (ed.),* William Bento publisher, 1989.

Camus A. 1955. *The myth of Sisyphus and other essays,* Justin, O'Brien (trans.). New York: Venture books.

Couzens D. 2009. Death, *in companion to phenomenology and existentialism:* Hubert, and Wralhal (eds.). Blackwell publishing.

Engels F. 1976. *Dialectics of Nature*, Clemens Duff (tr.), Moscow: progress publishers

Hartland J. 1951. *Plato as poet: A critical interpretation*, the Journal of Royal Institute of Philosophy, Vol. XXXVI. No. 96

Harvey P. *2005. An introduction to Buddhism*:*Teachings, history and practices*, *Cambridge University press.*

Heidgger M. 2000. *Introduction to metaphysics*, Gregory Friend, and Richard Plot (trans.) London: Yale University Press

Kant I. 1898. *Critique of Practical Reason and Other Works*. Abbott, Thomas Kingsmill (trans.) Longmans and Green: London, New York and Bombay

Shakespeare. 2004. *Hamlet.* Land mark of world literature, Cambridge University Press, New York, Melbourne, Madrid, Cape Town, Singapore, São Paulo